# በአብክመ

# የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ

## የ2017 በጀት ዓመት 1ኛው ሩብ ዓመት ሪፖርት

**መስከረም 2017 ዓ.ም**

**ባህር ዳር**

# 1 Contents


1. ማጠቃለያ ..... 2
2 መግቢያ ..... 3
3 የቢሮው ተልዕኮ ራዕይ እሴት ግቦችና አጠቃላይ ዓላማ ..... 5
4 በቅድመ ዝግጅት የተከናወኑ ተግባራት አፈጻጸም ..... 6
5 የአበይት ተግባራት አፈፃፀም ..... 9
5.1 የቁልፍ ተግባራት አፈጻጸም ..... 9
አመለካከት ..... 9
በክህሎት ..... 9
**በአደረጃጀት እና አሰራር** ..... 10
በግብዓት አቅርቦት ..... 11
5.2 የአበይት ተግባራት አፈጻጸም ..... 11
5.2.1 የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች አፈጻጸም ..... 11
5.2.2 የግንባታና ግንባታ ክትትል ሥራዎች አፈጻጸም ..... 18
5.3 የመ/ተ/ግብአት አቅርቦት ሥራዎች አፈጻጸም ..... 18
**ሐ. የመስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ስራ ግዥ** ..... 19
5.4 የተቋማት አስተዳደርና ጥገና ሥራዎች አፈጻጸም ..... 20
5.5 የዕ/በ/ዝ/ክ/ግ/ ሥራዎች አፈጻጸም ..... 21
5.6 የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች አፈጻጸም ..... 22
5.7 የሰው ኃብት ሥራዎች አፈጻጸም ..... 24
5.8 የግዥ፣ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር አፈጻጸም ..... 26
5.9 ባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አፈጻጸም ..... 28
6 የነበሩ ጥንካሬና ድክመቶች ..... 29
7 ያጋጠሙ ዋናዋና ችግሮችና የተወሰደ መፍትሄና የበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ..... 30


## 1. ማጠቃለያ

የክልሉን ህዝብ በመስኖ ልማት ዘርፍ ተጠቃሚ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የማልማት አቅማቸው 79,894.40 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ እና 542,981 ማህበረሰብ ተጠቃሚ

የሚያድርጉ በመንግስት አማካሪ ድርጅቶች ጥናታቸው በ2015 እና በፊት ተጀምረው ያደሩ በዚህ በጀት ዓመት 79,894.40 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ የ57 መስኖ ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዘዛይን ስራ በ2016 በጀት ዓመት ከነበሩበት 57.32% በመነሳት 22.25% በመፈጸም 79.56% ለማድረስ ታቅዶ በሩብ አመቱ 10.98% በመፈጸም 68.30% ማድረስ የተቻለ ሲሆን 29,688.20 ሄ/ር መሬት ማልማትና 208,140 ማህበረሰብ የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 29 (22 ግድቦች፤6 ጠለፋዎችና 2 ምንጭ ማጎልበት) ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ በሩብ አመቱ 2,556 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 6 ፕሮጀክቶች ተጠናቀዋል ፤

በበጀት ዓመቱ በዞኖችና ወረዳዎች 3,029.83 ሄ/ር የሚያለሙ እና 7,456 የክልሉን ህብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 53 የአነስተኛ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን በማጠናቀቅ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ታልሞ እየተሰራ ሲሆን ይህ ሩብ ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ የተከናወነ ተግባር የለም፡፡

በየደረጃው የሚገኘውን ፈጻሚ ሃይል በክህሎትና በአመለካከት በማብቃት በኩል በቢሮው አቅምና በልህቀት ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ኮርፖሬሽን ከወረዳ እስከ ቢሮ ድረስ በየሙያ ዘርፉ የሚሰለጥኑ 154 (መሀንዲስ 85 እና ቀያሽ 69) ሙያተኞች በበጀት ዓመቱ በባህር ዳር ማዕከል ስልጠናው ለመስጠት የተታቀደ ሲሆን ሙያተኞችን በመለየት ለ117 (መሀንዲስ 61 እና ቀያሽ 56) ሙያተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በዚህ ሩብ ዓመት 14,250 ሄ/ር መሬት የማልማት አቅም ያላቸው የ12 ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሰነድ ሙሉነት ግምገማ ተከናውኗል፡፡ በእቅድ ወጭ ለክላይሜት ስማርት ቫልዩ ዊት ቼይን የበጀት ድጋፍ የጥገናና ማስፋፊያ ሥራ የተመረጡ የ5 ፕሮጀክቶችን የዲዛይን ማሻሻያ እና የሰነድ ማስተካከል ተግባር ተከናውኗል፡፡

ከግንባታ እና ግንባታ ክትትል አኳያ 2017 ዓ.ም በዘላቂ ልማት ግብ ለመስኖ ፕሮጀከቶች ግንባታ የተመደበ በጀት 1,323,134,900.64 ብር ሲሆን ሌሎች ፕሮግራሞች ታሳቢ ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን የዝግጅት ምዕራፍ በመሆኑ ግንባታ አልተጀመረም፡፡

## 2 መግቢያ

የአማራ ብሔራዊ ክሌሊዊ መንገስት በ8º 45’ እስከ 13º 45’ ሰሜን የኬክሮስ እና በ35º 46’ እስከ 40º25’ ምሥራቅ የኬንትሮስ መስመር ውስጥ ይገኛል፡፡ የክልሉ ቆዳ ስፋት

157,126.83 ስኩዬር ኪሎ ሜትር ሲሆን የሀገሪቱን 15% ያህል ይሸፍናል፤ የክልሉ አስተዳደራዊ መዋቅር ሲታይ በአዲስ መልክ በ14 ዞን በ150 ወረዳ እና በ52 ከተማ አስተዳደር የተደራጀና በከተማ 5,197,996፤ በገጠር 18,351,002 በድምሩ 23,548,998 ህዝብ እንደሚኖር ይገመታል፡፡

የክልሉ የአየር ንብረት ሁኔታ ቆላ 33.66%፣ ወይና ደጋ 45.14%፣ ደጋ 20.37% እና በትንሹም ቢሆን ውርጫማ 0.83% ሲሆን መልካአ ምድራዊ አቀማመጡም ከባህር ወለል በላይ ከ500 እስከ 4,622 ሜትር የሚደርስ ነው፡፡ አማካኝ የሙቀት መጠኑም ከ20-25o ሴ.ግ ሲደርስ ዝቅተኛው 10o ሴ.ግነው፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑም ከ600-2000 ሚ.ሜ ዝናብ በዓመት ያገኛል፡፡የክልላችን ህዝብ በአብዛኛው በገጠር የሚኖርና የህይወት መሰረቱ ከምርታማ መሬትና ከዝናብ ውሀ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ለም መሬት በተለይም የውሀ ሀብት የሰው ልጅ ያለምንም ድካም ወይም በውስን ጥረት የሚያገኘው ከመሆኑም ባሻገር ሀብቱ በብዛት የጋራ የሆነና በተጠቃሚዎች መካከል ከፍተኛ የመጠቀም ሽሚያ ያለበት ነው፡፡ በዚህ ሀብት መመናመን የግብርና ምርትመቀነስ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የሰው ልጅ ህልውና ጭምር ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ነው፡፡

በሀገራችን ከተፈጥሮ ዝናብ ውጭ የውሀ ሀብትን ለመስኖ በስፋት መጠቀም የጀመረነው ከ1980 ዓ.ም በኋላ ሲሆን በደረሳ ተደጋጋሚ ድርቅ የተነሳ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በአማራጭነት የሚሰራ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ መሆኑን በመረዳት ከዝናብ ጥገኝነት ለመላቀቅና ችግሩን ከመሰረቱ ለመቀልበስ የሚያስችል ስራ ለመስራት የክልሉና የፌደራል መንግስት በሚመድቡት በጀት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡ በተደረገው ርብርብ በሁሉም አካባቢ በተመሳሳይ ደረጃ የተፈጸመ ባይሆንም ስራው በተሰራባቸው አካባቢዎች የህብረተሰብ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ እና ለብዙ አመታት የቆዩ የህብረተሰብ ጥያቄዎችንየመለሰ አበረታች ለውጥ ተመዝግቧል፡፡

የመስኖ መሰረተ ልማት የማስፋፋት ስራን በተሳካ ሁኔታ ጀምረነው እየሰፋ የመጣና የቆዬ የህብረተሰብ ጥያቄን የመለሰ ቢሆንም አሁንም በርካታ የሆነ የክልላችን አካባቢዎች የመስኖ አውታር ግንባታ ስራ አልተሰራባቸውም የህብረተሰብ ጥያቄወችም አልተመለሱም፡፡ከዚህ በተጨማሪም ሰፊ ምርታማ የሆኑ መሬቶችን በመስኖ ማልማት ሲችል በበጀት እጥረትና በተቋማዊ አቅም ውስንነት የተነሳ የታሰበውን ያህል ማከናወን አልተቻለም፡፡ በሌላ በኩል ተገንብተው ያለቁና ለመስኖበውሀ ተጠቃሚ ማህበራት የተላለፉ የመስኖ አውታሮችም ብዙ

አገልግሎት ሳይሰጡ የሚበላሹ ጥቂቶች ስላልሆነ ውጤታማ የአሰራር ስርአቶችን በመዘርጋትና ተቋማዊ ለውጥና ጥንካሬ በመፍጠር ችግሩን መፍታት አስፈላጊ ነው፡፡

በዝናብ እጥረት ምክንያት የሚመጣው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ችግር ውስብስብ ከመሆኑ አንጻር በሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመፍታት የመስኖ ስራን የርብርብ ማዕከል አድርጎ ማስቀጠል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ በፊት በመስኖ መሰረተ ልማት ረገድ የተገኙ መልካም ልምዶችን በመቀመር እጥረቶችን ደግሞ በአግባቡ በመገምገም በፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት አሁንም ያልተፈቱ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተቶች በመለየት በተከታታይ ውይይቶችና ሙያዊ ስልጠናዎች እንዲፈቱ በማድረግ የመስኖ መሰረተ ልማት ስራዎች በትጋት እየተሰራ ሲሆን የ2017 በጀት ዓመት 1ኛው ሩብ ሪፖርት እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

## 3 የቢሮው ተልዕኮ ራዕይ እሴት ግቦችና አጠቃላይ ዓላማ

### ርዕይ

በ2023 ዓ/ም ክልሉ ያለዉን እምቅ የመሬት ሃብት በመስኖ በማልማት የክልላችንን የምግብ ሉአላዊነት ተረጋግጦ ማየት፤

**ተልዕኮ**

በክልሉ ያለውን ሰፊ የመስኖ ልማት አቅም በመለየት አሳታፊና ጥራት ያለው የጥናት፣ ዲዛይን እና ግንባታ ስራ በማከናወን፤ ተስማሚ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመስኖ ተቋማትን በማስተዳደርና ለቆላማ አካባቢዎች ልማት ልዩ ትኩረት በመስጠት ህብረተሰቡን በዘላቂነት እና በፍትሃዊነት ተጠቃሚ ማድረግ፤

**እሴቶች**

- ፍትሃዊነት
- አሳታፊነት
- ታማኝነት
- ቅንነት
- አገልጋይነት
- በቡድን መስራት
- ሆኖ መገኘት

**የቢሮው አጠቃላይ ዓላማ**

የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ዘላቂ የመስኖ ዉሀ እንዲኖር ማስቻል እና አጠቃቀሙን ዘመናዊ በማድረግ የግብርና ምርትና ምርታማነትን በመጨመር በክልሉ በቤተሰብ ደረጃ ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ብሎም ድህነትን ለመቀነስ የመስኖ ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጾ እንዲኖረዉ ማድረግ ፡

# 4 በቅድመ ዝግጅት የተከናወኑ ተግባራት አፈጻጸም

- የቢሮውን የ8 አመቱን የልማትና የመልካም አስተዳድር ዕቅድ መነሻ በማድረግ የቢሮው የ5 ዓመትና ዓመታዊ ዕቅድ እና ፤የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ተዘጋጅቶ ተገምግሞ ተልኳል፤
- በቢሮው አቅምና በልህቀት ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ኮርፖሬሽን ከወረዳ እስከ ቢሮ ድረስ በየሙያ ዘርፉ የሚሰለጥኑ ሙያተኞችን በመለየት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- በ2016 በጀት ዓመት በወረዳና ዞኖች አቅም የጥናት ዲዛይን ስራ ለሚሰራላቸው 15 አዲስ እና የክለሳ ሥራ ለሚሰራቸው 99 ነባር ፕሮጀክቶች አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ስራ በመፈፀም የቢሮና የመስክ ስራውን እንዲያከናውኑ ከዞኖች ጋር በመነጋገር ስራ ማስጀመር ተችሏል፡፡ በየሙያ ዘርፉ ስልጠና የሚሰጥባቸውን ርዕሶችን የመለየትና የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡
- በ2016 ለተሰሩ ስራዎች እቅድ አፈጻጸም (ፊዚካልና ፋይናንሻል) በዝርዝር መገምገም ፣ የነበሩ ጥሩ ተሞክሮዎችና ክፍተቶች ላይ ከፍጻሚው ጋር ውይይት ማድረግና የወደፊት ሰራዎች ላይ አቅጣጫ የማስቀመጥ ሰራ ተሰርቷል
- 2017 በመሪ ዕቅዱ ላይ ዉይይት በማድረግ የዳይሬክቶሬቱን ዓመታዊ እቅድ ከበጀት አንጻር የመከለስ ስራ በመሰራት የጋራ ተደረጓል፣
- ባለሙያዎችን ለየቀጠናው የግንባታ ፕሮጀክቶች በመመደብ የ2017 የመጀመሪያውን ግማሽ ዓመት ዕቅድ በውጤት ተኮር ስርዓት ወደ ፈጻሚው ማውረድና የስራ ውል መፈረም፣
- ለተሰሩ ስራዎች የክፍያ ጥያቄዎችን 32,566,735.00 ብር የሚሆን 23 የክፊያ ሰነዶች የማዘጋጀትና የማጸደቅ ሰራ ተሰርቷል፣
- ሦስት (3) በምግብ ስርዓት ማጠናከሪያ ፕሮግራም በጀት የሚገነቡ፣አራት (4) በዘላቂ ልማት ግብ በጀት የሚገነቡ እንዲሁም አራት (4) በአፍሪካ ልማት ባንክ በጀት የሚገነቡ አጠቃላይ 11 ፕሮጀከቶች ለጫርታ እንዲወጡ አሁናዊ የዋጋ ግምትና የዶክምንት ክለሳ በማድረግና አሰፈላጊውን መረጃ በማሟላት ለሚመለከተው የሰራ ክፍል ተልኳል፣
- በግንባታ ላይ የነበሩና የዲዛይን ማሻሻያ የሚያስፈለጋቸው 3 ፕሮጀክቶች /ሰርወልድ፣ ጀልደቲና ማመጫ ገዳም ፕሮጀክቶችን የዲዛይን ክለሳ ስራ በመስራት ለአማካሪ መልስ ተሰጥቷል፣
- ከፍተኛ የዲዛይና ማሻሻያ የተደረገለት የፈጣም ፕሮጀክት ከአማካሪ ድርጅት ጋር በጋራ በመሆን የዲዛይን ማስተካከያ በማድረግ ለዋጋ ድርድር ለግብዓት አቅርቦት ተልኳል፣
- የመልሶ መቋቋም ፕሮጀክቶችን ዝርዝር መረጃ መሰብሰብ በ2017 ፈጥነው ወደ ግንባታ የሚገቡ 8 ፕሮጀክቶች መረጃው ለፈንድ ጽ/ቤት ተልኳል፣
- በ2016 በጀት ዓመት በወረዳና ዞኖች አቅም የጥናት ዲዛይን ስራ ለሚሰራላቸው 15 አዲስ እና የክለሳ ሥራ ለሚሰራቸው 99 ነባር ፕሮጀክቶች አስፈላጊውን የቅደድመ

ዝግጅት ስራ በመፈፀም የቢሮና የመስክ ስራውን እንዲያከናውኑ ከዞኖች ጋር በመነጋገር ስራ ማስጀመር ተችሏል፡፡

- በ2016 የፕሮጀክቶች የስራ አፈጻጸም ሪፖርትና የ2017 እቅድ ላይ የክልሉ የአማካሪና ተቋራጭ የልማት ድርጅቶች ሃላፊዎችና የክልል ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት የ3ዮሽ ውይይት ተደርጓል፣
- በሽድፕ በጀት በግንባታ ላይ የነበሩና ውላቸው የተቋረጡ የ8 መስኖ ፕሮጀክቶችን ከዞን በቀረበው መረጃ መሰረት የቀሪ ስራ አሁናዊ የዋጋ ግምት በመስራት የሚያስፈልግ የበጀት መጠን ለግብርና ቢሮ ተልኳል፣
- የ90 ቀናት እቅድ በማቀድ በቢሮው ለገጠር ልማት ክላስተር ማስተባበሪያ እንድላክ ተደርገጓል
- የዳይሬክቶሬቱን ዋናዋና ተግባራት በቁልፍ ተግባር አመላካች (KPI) በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፣
- በግንባታ ላይ ከፍተኛ ችግሮችን በመለየት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት እቅድ ተዘጋጅቷል'
- ክረምቱ በመገባደዱ ማስገባት የሚችሉ 6 ፕሮጀክቶች /ደባሪ ቴክኖሎጂ፣ጃሊያ፣ አባቡልቻ፣ ሮቢት፣ ውዲ እና ማይስ/ ፕሮጀክቶች የግንባታ ግብዓት የማስገባት ስራ ተጀምሯል፣
- ከ2016 ሊ.ም ሂሳብ ከገንዘብ ቢሮ ጋር በመዝጋት ለ2017 ሊ.ም የተመደበ በጀት እና የሚያልፉ ሂሳቦችን ምዝገባ ማካሄድ፡የፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነትን ለማሳደግ ሂሳቦችን በኮዳቸው በሌጀር እና በአይቤክስ ተመዝግቦ ክትትል ማድረግ፤
- አመታዊ የግዥ ፍላጎት በየአይተማቸው ማደራጀት በአዋጅ፣በመመሪያና የግዥ አሰራርን መሰረት ያደረገ መ/ቤቱን ውጤታማ በሚያደርግ መልኩ ቀልጣፋና ጥራት ያለው ግዥ እንዲፈፀም የግዥ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፤
- ቋሚ እና አላቂ ንብረቶችን ቆጠራ በማካሄድ ንብረቶችን በመዝገብ አደራጅቶ ተይዟል፡ ተሽከርካሪ በወቅቱ ሰርቪስ እንዲያገኙ በማድረግ ስምሪት ተሰጥቷል፤
- 15 አዲስ የጥገና ፕሮጀክቶችን የነጠላ ዋጋ ተከላና የግንባታ ንድፍ ስራ እየተከናወነ ይገኛል፤
- ዞን እና ለወረዳ የአቅም ግንባታ ስራ ለማከናወን የሥልጠና ዕቅድ ተዘጋጅቷል፤

- የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች የማህበራት የሂሳብ አያያዝ እና የኦዲት መመሪያ ለዞኖች ማብራሪያ ተሰጥቷል፤
- ለባለሙያዎች የስራ ክፍፍል ተደርጓል ለሁሉም ሰራተኞች ውጤት ተኮር ውል እንዲይዙ ተደርጓል፤
- ሁሉም ዞኖች የመስኖ ቦይ ጠረጋ በልዩ ትኩረት እንዲያከናዉኑ መመሪያ ተሰጥቷል፡፡
- በግንባታ ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር እንዲኖራቸው ከዞኖች ጋር የጋራ መግባባት ተደርሷል፡፡

# 5 የአበይት ተግባራት አፈፃፀም

## 5.1 የቁልፍ ተግባራት አፈጻጸም

**አመለካከት**

- በየወሩ የአመለካከት ክፍተቶችን ለማረም የሚደረገው ጥረት እየተሻሻለ መምጣቱ
- በአመለካከት ችግር ያለባቸውን ፈፃሚች ለማስተካከል በሥራ ክፍሉ በሚደረገው ውይይት የነቃ ተሳትፎ ማድረግ መቻል

**በክህሎት**

ቢሮው ከልህቀት ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር ውል በመውሰድ በዞንና ክልል ደረጃ ለሚገኙ ባለሙያዎች በምህንድስናና ሴክቶሪያል የሙያ ዘርፎች ከ25-30 ለሚደርስ ቀናት እንዲሰለጥኑ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተጠናቆ ስልጠናው ተሰጥቷል፡፡

ሠንጠረዥ-1 የሥልጠና መረጃ

| ተ.ቁ | ስልጠና የሚሰጥበት ርዕስ | ስልጠና የሚሳተፉ (እቅድ) | | | | ስልጠና የተሳተፉ | | | አፈጻጸም በ ( %) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ዞን | ወረዳ | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| 1 | መሰረታዊ ምህንድስና | 4 | 7 | 78 | 89 | 52 | 9 | 61 | 68.54 |
| 2 | ቅየሳና ካርታ ስራ | 4 | 13 | 56 | 73 | 38 | 18 | 56 | 76.71 |
| | ድምር | 8 | 20 | 134 | 162 | 90 | 27 | 117 | 72.22 |

በየደረጃው የሚገኘውን ፈጻሚ ሃይል በክህሎትና በአመለካከት በማብቃት በኩል በቢሮው አቅምና በልህቀት ዲዛይንና ቁጥጥር ሥራዎች ኮርፖሬሽን ከወረዳ እስከ ቢሮ ድረስ በየሙያ ዘርፉ የሚሰለጥኑ 154 (መሀንዲስ 85 እና ቀያሽ 69) ሙያተኞች በበጀት ዓመቱ በባህር ዳር

ማዕከል ስልጠናው ለመስጠት የተታቀደ ሲሆን ሙያተኞችን በመለየት ለ117 (መሀንዲስ 61 እና ቀያሽ 56) ሙያተኞች ስልጠና ተሰጥቷል ይህም የእቅዱን 72.22 % ማከናወን ተችሏል ፡፡

**<u>በስልጠናው የተገኘ ውጥት</u>**

1. በክልሉ ውስጥ ያለውን እምቅ የመስኖ አቅም መለየት እና ቅደም ተከተል በማውጣት ለጥናትና ዲዛይን ዝግጁ እንዲሆኑ ይረዳል
2. እንደ ተቋም ወጥነት ያለው አሰራር እንዲኖር ምቹ የሆነ መደላድል መፈጠሩ
3. ባለሙያዎችን በሙያቸው ብቁ እንዲሆኑ ከማስቻሉም ባሻገር ለተቋሙ የመቆርቆርና የባለቤትነት ስሜት መፍጠሩ
4. በጥናት እና በዲዛይን ላይ የተመሰረተ የንድፍ ሥራ እንዲዘጋጅ ያስችላል፤
5. የስራ ስፍር መጠን በሚዘጋጅበት ወቅት በመሬት ላይ የተረጋገጠ ስለሚሆን ልኬታን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ያስችላል ይህም ግልጽና የተሳለጠ የጨረታ ሂደት እንዲኖር ይግዛል፤
6. ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ በሚገቡበት ወቅት በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የስራ ለውጦች እና የዲዛይን የማሻሻያ ሥራዎችን ይቀንሳል በዚህም የተነሳ የሚፈጠሩ አላስፈላጊ የለውጥ ሥራ ወጪዎችን እንዲሁም የግንባታ መጓተትን እንዳይሮ ይረዳል፤
7. ማህበረሰብ አሳታፊ የጥናትና ዲዛይን ሥራ መስራትና በግንባታ ወቅትም እንዲከታተሉ በማድረግ የባላቤትነት ስሜት እንዲፈጥር ስለሚረዳ ይህም የመስኖ መሰረተ ልማት አውታሮችን በቅርበት እንዲከታተሉና እንዲንከባከቡ ስለሚያደርግ ፕሮጀክቶቹ በዘላቂነት እንዲያገለግሉ ያስችላል ፤የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራትን በማቋቋም ፍትሃዊ የውሃ ተጠቃሚነት እና ሊከሰቱ የሚችሉ አለመግባባቶችና ግጭቶች እንዳይከሰቱ ያደርጋል

**በአደረጃጀት እና አሰራር**

- ለሁሉም ቡድኖች ፈፃሚዎች የውጤት ተኮር እቅድ በማዘጋጀትና ግንዛቤ በመፍጠር ተፈራርሞ የአፈፃፀም ውጤት በማኔጅመንት በማጸደቅ ውጤት እንዲሞላ እና ቀሪ ስድስት ወር ውል  እንዲያዝ ተደርጓል ፡፡
- ሁሉም ባለሙያወች ፈፃሚዎች የስራ እቅድና የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት ወደ ስራ የተገባበትና ውጤት የታየበት መሆኑ  ምቹ  የስራ ሁኔታ መፍጠር የሚያስችል አበረታች ጥረት መታየቱ፡፡

**በግብዓት አቅርቦት**

❖ አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ደንበኞችን ያለምንም ቅሬታ ለማስተናገድ የሚደረገው ጥረት እየተሸሻለ መምጣትና የጋራ መግባባት መፈጠሩ፤ለሥራ የሚያስፈልጉ ግብአቶች በአብዛኛው የተሟሉ መሆን

## 5.2 የአበይት ተግባራት አፈጻጸም

### 5.2.1 የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች አፈጻጸም

**ግብ:** በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ በዕውቀት እና ፀጋዎች እንዲሁም የክልሉን አቅም መሰረት ባደረገና ባገናዘበ መልኩ የመስኖ መሰረተ ልማቱ የሚሳለጥበትን የገፀ-ምድርና የከርሰ-ምድር የውሃ ሃብትን ጥናትና ዲዛይን በመስራትና ወደ ልማት እንዲገቡ በማድረግ የመስኖ ልማቱን ማፋጠን ፡፡

**ዝርዝር ተግባራት**

❖ በዚህ በጀት ዓመት 79,894.40 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ የ57 መስኖ ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዘዛይን ስራ በ2016 በጀት ዓመት ከነበሩበት 57.32% በመነሳት 22.25% በመፈጸም 79.56% ለማድረስ ታቅዶ በሩብ አመቱም 6.66% ለመስራት ታቅዶ 10.98% መፈጸም የተቻለ ሲሆን አሁን በአጠቃላይ 68.30% ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 2- የ57 ነባር ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ሥራ ዝርዝር ዕቅድ አፈፃፀም**

| ተ.ቁ. | የፕሮጀክት ስም | የፕሮጀክቱ መገኛ ቦታ | | | የማልማት አቅም ሄ/ር | የፕሮጀክት አይነት | በ2016ዓ.ም የተደረሰበት | ጠቅላላ ቀሪ ስራ | የ2017 በጀት ዓመ | የ2017 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | እቅድ | | ክንውን | |
| | | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ | | | | | | 1ኛ ውሩ | እስከ ዚህ ሩብ | በዚህ ሩብ | እስከ አሁን የተደ |

| | | | | | | | | | ት ዕቅ ድ | ብ ዓ መ ት | ዓመ ት | ዓ መ ት | ረሰበት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዞሪት ግድብ | ደ/ጎን ደር | እስቴ | ምክሬ | 860 | ግድብ | 97 | 3 | 100 | 3 | 100 | 3 | 100 |
| 2 | ኮንኮዝ ግድብ | ደ/ጎን ደር | ፎገራ | ዘንግ | 300 | ግድብ | 97 | 3 | 100 | 3 | 100 | 3 | 100 |
| 3 | አሂሪት ግድብ | ደ/ጎን ደር | አንዳቤት | | 250 | ግድብ | 97 | 3 | 100 | 3 | 100 | 3 | 100 |
| 4 | ጥቁር ውሃ ግድብ | ደ/ጎን ደር | እብናት | መችና | 2000 | ግድብ | 75 | 25 | 81.25 | 10 | 81.25 | 10 | 85 |
| 5 | ዝሃር ግድብ | ደ/ጎን ደር | ስማዳ | እንባ ጣመ | 250 | ግድብ | 75 | 25 | 81.25 | 10 | 81.25 | 10 | 85 |
| 6 | ወርቃ ግድብ | ደ/ጎን ደር | ፎገራ | አለም በር ዙሪያ | 300 | ግድብ | 97 | 3 | 100 | 3 | 100 | 3 | 100 |
| 7 | አምላክ ብርሃን ግድብ | ደ/ጎን ደር | እስቴ | ልጫ | 3500 | ግድብ | 75 | 25 | 81.25 | 10 | 81.25 | 10 | 85 |
| 8 | አሲዳ ግድብ | ደ/ወ ሎ | አምሐራ ሳይንት | ሽንጎ ደፍር | 200 | ግድብ | 90 | 10 | 92.5 | 2 | 92.5 | 2 | 92 |
| 9 | ሚጫ ግድብ | ደ/ወ ሎ | ጃማ | /ኤልያስ ዋሻ | 700 | ግድብ | 95 | 5 | 100 | 1 | 100 | 1 | 96 |
| 10 | የጅምባር ግድብ | ሰ/ሸዋ | ሞጃና ወደራ | ሃይሶፌ | 500 | ግድብ | 90 | 10 | 92.5 | 5 | 92.5 | 5 | 95 |
| 11 | ጎሽጌ ጠለፋ | ሰ/ሸዋ | ሞጃና ወደራ | ጎሽጌ ዙብ አምባ | 100 | ጠለፋ | 90 | 10 | 92.5 | 5 | 92.5 | 5 | 95 |
| 12 | ጋብሬል ግድብ | ደ/ወ ሎ | መካነሰላም | አባድር (011) | 700 | ግድብ | 90 | 10 | 92.5 | 0 | 92.5 | 0 | 90 |
| 13 | ለገኮራ ጠለፋ | ደ/ወ ሎ | ቦረና | ጨሮካዲ ስ | 500 | ጠለፋ | 90 | 10 | 92.5 | 0 | 92.5 | 0 | 90 |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | የሹም ፓምፕ | ደ/ወሎ | ወግዲ | ሌንጬ (029) | 400 | ግድብ ፓምፕ | 90 | 10 | 92.5 | 5 | 92.5 | 5 | 95 |
| 15 | አምቦፈረስ ግድብ | ደ/ወሎ | መቅደላ | ሃሮጌ (017) | 150 | ግድብ | 91 | 9 | 93.25 | 0 | 93.25 | 0 | 91 |
| 16 | ሙላቱ ጎራ ግድብ | ደ/ወሎ | አልቡኮ | 09 (ነጺ) | 300 | ግድብ | 90 | 10 | 92.5 | 0 | 92.5 | 0 | 90 |
| 17 | ተሰንቆ ግድብ | ደ/ወሎ | ደላንታ | | 1000 | ጠለፋ | 91 | 9 | 93.25 | 4 | 93.25 | 4 | 95 |
| 18 | የዳ ግድብ | ምስ/ጎጃም | አነደድ እና ጎዛመን | ጭንቦርድ | 4,000 | ግድብ | 55 | 45 | 60 | 5 | 60 | 5 | 60 |
| 19 | ጠይሞ | ምስ/ጎጃም | ቢቡኝ እና ደጋ ዳሞት | ገና መምቻ | 800 | ግድብ | 35 | 65 | 40 | 0 | 40 | 0 | 35 |
| 20 | ኮሜድ | ምስ/ጎጃም | ማቻከል | አንስላላ | 3,500 | ግድብ | 55 | 45 | 60 | 0 | 60 | 0 | 55 |
| 21 | ቡጥላ ግድብ | ምዕ/ጎጃም | ቋሪት | ቡጥላ | 4,500 | ግድብ | 35 | 65 | 40 | 5 | 40 | 5 | 40 |
| 22 | ወረመት | ምዕ/ጎጃም | ደቡብ ሜጫ | ተክሌ ተራራ | 1,700 | ግድብ | 40 | 60 | 46.25 | 45 | 46.25 | 45 | 85 |
| 23 | ባምብላ | ማዕ/ጎንደር | ታች አርማጮ | ካችካም | 3,200 | ግድብ | 40 | 60 | 46.25 | 50 | 46.25 | 50 | 90 |
| 24 | ትልቅ ወንዝ | ሰ/ጎንደር | ጃንአሞራ | ረቡገበያ | 700 | ግድብ | 70 | 30 | 77.5 | 30 | 77.5 | 30 | 100 |
| 25 | ሃምሳ ፈጅ | ማ/ጎንደር | ዳባት | ዶሮማ ማይ | 550 | ግድብ | 85 | 15 | 88.75 | 0 | 88.75 | 0 | 85 |
| 26 | ዓንጊት ግድብ | ምዕ/ጎንደር | ቋራ | ዱባባ | 6,000 | ጠለፋ | 85 | 15 | 88.75 | 0 | 88.75 | 0 | 85 |
| 27 | መርሆም ግ | ምዕ/ጎንደር | ቋራ | ሰልፈረዲ | 450 | ግድብ | 30 | 70 | 35 | 5 | 35 | 5 | 35 |
| 28 | ቡሶ ግድብ | ደ/ወሎ | ለጋምቦ | 05 የትምራ እና 06 | 1,300 | ግድብ | 30 | 70 | 35 | 5 | 35 | 5 | 35 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 29 | ደርባ ግድብ | ደ/ወሎ | ለጋምቦ | 020 ደረባ | 1,164 | ግድብ | 30 | 70 | 35 | 15 | 35 | 15 | 45 |
| 30 | ሰቲጋ ግድብ | ደ/ወሎ | መቅደላ | ደብረ ዘይት ሃሮይ | 526 | ግድብ | 30 | 70 | 35 | 0 | 35 | 0 | 30 |
| 31 | የስጋ ግድብ | ደ/ወሎ | መቅደላ | ከብቲያኽና አደጉ | 1,490 | ግድብ | 40 | 60 | 45 | 20 | 45 | 20 | 60 |
| 32 | ሰውር ግድብ | ደ/ወሎ | ጃማ ደጎሎ | መቻ እና ቦረን | 426 | ግድብ | 30 | 70 | 35 | 5 | 35 | 5 | 35 |
| 33 | ወንጭት | ሰ/ሸዋ | ሚዳ ወረሞ | ደንጎሬ | 3,200 | ግድብ | 55 | 45 | 66.25 | 0 | 66.25 | 0 | 55 |
| 34 | ሹም ገደል | ደ/ወሎ | ከለላ | 15 | 4,000 | ግድብ | 30 | 70 | 35 | 0 | 35 | 0 | 30 |
| 35 | ወልገሀ | ደ/ወሎ | ከለላ | 20 | 4,000 | ኢንቴክ | 30 | 70 | 35 | 0 | 35 | 0 | 30 |
| 36 | ወረሌንጫ | ኦሮሞ ብ/ዞን | ጅሌ ጥሙጋ | ወረሌንጫ | 200 | ግድብ | 35 | 65 | 40 | 0 | 40 | 0 | 35 |
| 37 | ቡረቃ ጂሌ | ኦሮሞ ብ/ዞን | ቡርቃ (ጅሌ ጥሙጋ) | ፋጢኩ መቡሪ | 150 | ኢንቴክ + ፓምፕ | 28 | 72 | 33.5 | 7 | 33.5 | 7 | 35 |
| 38 | ዛላ ግድብ | ሰ/ሸዋ | መንዝ ጌራ ምድር | 12 | 131 | ግድብ | 35 | 65 | 41.25 | 0 | 41.25 | 0 | 35 |
| 39 | ዋቃ ግድብ | ሰ/ሸዋ | መንዝ ማማ | 4 | 1,325 | ግድብ | 35 | 65 | 40 | 0 | 40 | 0 | 35 |
| 40 | ጀማ ፈዘዝ | ሰ/ሸዋ | መርሐቤቴ | አፈዘዝ | 1,000 | ግድብ | 35 | 65 | 40 | 0 | 40 | 0 | 35 |
| 41 | ጀንበሪያ | ሰ/ሸዋ | ሃገረ ማሪያም | ቅዱሰጌ | 258 | ግድብ | 35 | 65 | 41.25 | 55 | 41.25 | 55 | 90 |
| 42 | ገደል ውሃ | ሰ/ሸዋ | መንዝ ላሎ | ሰስጋ | 1,270 | ኢንቴክ + ፓምፕ | 30 | 70 | 35 | 0 | 35 | 0 | 30 |
| 43 | ፋፋቴ | ሰ/ሸዋ | አንኮበር | ደረፎ | 182 | ምንጭ ማጎልበት | 90 | 10 | 92.5 | 0 | 92.5 | 0 | 90 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 44 | አይራራ | ሰ/ሸዋ | አንኮበር | ጨፋ | 222 | ግድብ | 30 | 70 | 35 | 60 | 35 | 60 | 90 |
| 45 | ገምዙ | ምዕ/ጎንደር | መተማ | ወዲገምዙ | 146 | ምንጭ ማጎልበት | 90 | 10 | 92.5 | 10 | 92.5 | 10 | 100 |
| 46 | ወለህ | ዋግህምራ | ሰ/ዙሪያ | ወለህ | 600 | ኢንቴክ | 90 | 10 | 92.5 | 0 | 92.5 | 0 | 90 |
| 47 | ቆጠት ግድብ | ሰ/ጎጃም | ይልማና ዴንሳ | ጎቤ | 500 | ጠለፋ | 0 | 100 | 100 | 90 | 100 | 90 | 90 |
| 48 | የዛት ግድብ | ሰ/ጎጃም | ይልማና ዴንሳ | እነጋዴ | 1500 | ግድብ | 0 | 100 | 25 | 90 | 25 | 90 | 90 |
| 49 | ቦገና ግድብ | ምስ/ጎጃም | አዋበልና ጎዛምን | የቦቅላ | 2,000 | ግድብ | 60 | 40 | 70 | 30 | 70 | 30 | 90 |
| 50 | ግልንብጥ | ምዕ/ጎጃም | ደንበጫ | ዋድ | 1,000 | ግድብ | 90 | 10 | 92.5 | 0 | 92.5 | 0 | 90 |
| 51 | ጋንትና ግድብ + ግፊት | ምዕ/ጎጃም | ደንበጫ | ዋድ | 1,300 | ግድብ | 90 | 10 | 92.5 | 0 | 92.5 | 0 | 90 |
| 52 | ሱሃ ግድብ | ምስ/ጎጃም | እነማይ | ደብረ ገነት | 6,000 | ግድብ | 30 | 70 | 35 | 35 | 35 | 35 | 65 |
| 53 | ዚያ ግድብ | ምስ/ጎጃም | ደብረ ወርቅ | ተንጉማ ወፍናን | 2,000 | ግድብ | 32 | 68 | 36.5 | 0 | 36.5 | 0 | 32 |
| 54 | ጠምበለል | ምዕ/ጎጃም | ደንበጫ | ጃጂራብ | 2,000 | ግድብ | 32 | 68 | 36.5 | 0 | 36.5 | 0 | 32 |
| 55 | ኩራር | ምስ/ጎጃም | ደጀን | ኩራር | 95 | ግድብ | 32 | 68 | 36.5 | 0 | 36.5 | 0 | 32 |
| 56 | እንግች ግድብ | ምስ/ጎጃም | አነደድ | ሰንደባ | 4,000 | ግድብ | 20 | 80 | 27.5 | 0 | 27.5 | 0 | 20 |
| 57 | ዋንቃ/ጎጣ | ደ/ጎንደር | እስቴ | በርኩት | 500 | ግድብ | 23 | 77 | 29.75 | 0 | 29.75 | 0 | 23 |
| | ድምር | | | | 79,894.40 | | 57.32 | 42.68 | 22.25 | 6.66 | 63.98 | 10.98 | 63.98 |

በበጀት ዓመቱ በአማከሪ ድርጅቶች የጥናትና ዲዛየይን ከሚሰሩ 57 ፕሮጀክቶች ውስጥ 29,688.20 ሄ/ር መሬት ማልማትና 208,140 ማህበረሰብ የመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ የሚያደርጉ 29 (22 ግድቦች፣6 ጠለፋዎችና 2 ምንጭ ማጎልበት) ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ታቅዶ በሩብ አመቱ 2,556 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 6 ፕሮጀክቶች ተጠናቀዋል ፤

**ሠንጠረዥ 3- በሩብ አመቱ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ዝርዝር**

| ተ.ቁ | ዞን | ፕሮጀክት | የማልማት አቅም ሄ/ር | በ2016 ዓ.ም የተደረሰበት | የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ | የ2017 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | እቅድ | | ክንውን | |
| | | | | | | 1ኛው ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከ አሁን የተደረሰበት |
| 1 | ደ/ጎንደር | 4 | 1,710 | 97 | 3 | 3 | 97 | 3 | 100 |
| 2 | ሰ/ጎንደር | 1 | 700 | 70 | 30 | 7.5 | 70 | 30 | 100 |
| 3 | ምዕ/ጎንደር | 1 | 146 | 90 | 10 | 2.5 | 90 | 10 | 100 |
| | **ድምር** | **6** | **2,556** | **57** | **43** | **13** | **57** | **43** | **100** |

- በበጀት ዓመቱ እንደ ዳይሬክተር የ110 ፕሮጀክቶችን (በአማካሪ ድርጅቶች 57 እና በወረዳዎችና ዞኖች ደግሞ 53) አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ፕረሮጀክቶችን የመጀመሪያ ረቂቅ እና የመጨረሻ ዝርዝር የጥናትና ዲዛይን ሰነድ ሙሉነት ግምገማ በማካሄድ በቢሮው በኩል ተቀባይነት ያገኙትንና ያለፉትን ፕሮጀክቶችን ወደ ሚመለከተው ዳይሬክተር ለማስተላለፍ እንዲያመች ታልሞ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- በዚህም መሰረት በዚህ ሩብ አመት 14250 ሄ/ር የመልማት አቅም ያላቸው በልህቀት የጥናትና ዲዛይነ ኮረፖሬሽን የጥናትና ዲዛይን የተሰራላቸው 12 ፕሮጀክቶች የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ ቀርቦ ግምገማ ተካሂዶ መታየትና መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች እንዲታረሙ ለኮርፖሬሽኑ በልም ቅጅ ግብረመለስ ተሰጥቶታል፡፡

## ሠንጠረዥ4. የፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ስራ የሰነድ ግምገማ ዕቅድ አፈፃፀም

| ተ.ቁ. | የፕሮጀክት ስም | የፕሮጀክቱ መገኛ ቦታ | | | የማ/አ ቅም ሄ/ር | የፕሮጀክት አይነት | በ2016ዓ.ም የተደረ ሰጸበት | ጠቅላላ ቀሪ ስራ | የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ | የ2017 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | እቅድ | | ክንውን | |
| | | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ | | | | | | 1ኛው ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከ አሁን የተደረ ሰበት |
| 1 | ጥቁር ውሃ ግድብ | ደ/ጎንደር | እብናት | መችና | 2000 | ግድብ | 97 | 3 | 3 | 3 | 100 | 3 | 100 |
| 2 | ዝሃር ግድብ | ደ/ጎንደር | ስማዳ | እንባ ጣመ | 250 | ግድብ | 75 | 25 | 25 | 6.25 | 81.25 | 10 | 85 |
| 3 | አምላከ ብርሃን ግድብ | ደ/ጎንደር | እስቴ | ልጫ | 3500 | ግድብ | 75 | 25 | 25 | 6.25 | 81.25 | 10 | 85 |
| 4 | አሲዳ ግድብ | ደ/ወሎ | አምሐራ ሳይንት | ሽንጎ ደፍር | 200 | ግድብ | 90 | 10 | 10 | 2.5 | 92.5 | 2 | 92 |
| 5 | ሚጫ ግድብ | ደ/ወሎ | ጃማ | /ኤልያስ ዋሻ | 700 | ግድብ | 95 | 5 | 5 | 5 | 100 | 1 | 96 |
| 6 | የጅምባር ግድብ | ሰ/ሸዋ | ሞጃና ወደራ | ሃይሶፌ | 500 | ግድብ | 90 | 10 | 10 | 2.5 | 92.5 | 5 | 95 |
| 7 | ጎሽጌ ጠለፋ | ሰ/ሸዋ | ሞጃና ወደራ | ጎሽጌ ዙብ አምባ | 100 | ጠለፋ | 90 | 91 | 92 | 93 | 183 | 95 | 96 |
| 8 | የሹም ፓምፕ | ደ/ወሎ | ወግዲ | ሌንጮ (029) | 400 | ግድብ | 90 | 10 | 10 | 2.5 | 92.5 | 5 | 95 |
| 9 | ተሰንቆ ግድብ | ደ/ወሎ | ደላንታ | | 1000 | ጠለፋ | 91 | 9 | 9 | 2.25 | 93.25 | 4 | 95 |
| 10 | ወረመት | ምዕ/ጎጃም | ደቡብ ሜጫ | ተክሌ ተራራ | 1700 | ግድብ | 40 | 60 | 25 | 6.25 | 46.25 | 45 | 85 |
| 11 | ባምብላ | ማዕ/ጎንደር | ታች አርማጮ | ካችካም | 3200 | ግድብ | 40 | 60 | 25 | 6.25 | 46.25 | 50 | 90 |
| 12 | ትልቅ ወንዝ | ሰ/ጎንደር | ጃንአሞራ | ረቡገበያ | 700 | ግድብ | 70 | 30 | 30 | 7.5 | 77.5 | 30 | 100 |
| | ድምር | | | | 14,250 | | 78.58 | 28.17 | 22.42 | 11.94 | 90.52 | 21.67 | 100.3 |

### 5.2.2 የግንባታና ግንባታ ክትትል ሥራዎች አፈጻጸም

- በአጠቃላይ በዚህ በጀት ዓመት የተመደበውን በጀት በአግባቡ ለመጠቀም በሚያስችል ሁኔታ የግንባታ ስራዎችን በእቅድ ተይዘዋል። ለ2017 ዓ.ም በዘላቂ ልማት ግብ ለመስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ የተመደበ በጀት 1,323,134,900.64 ብር ሲሆን ሌሎች ፕሮግራሞች ለወደፊት ታሳቢ የሚደረግ ነው።
- በክልሉ ውስጥ የሚከናወኑ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የመስኖ ግንባታ ስራዎችን የሚያከናውን ሲሆን እነዚህ ስራዎች በክልል፡ በዞን፣ በአማካሪና በተቋራጭ ድርጅቶች የሚሰሩ ናቸው፤ ሪፖርቱ የሩብ አመቱን ክልላዊ የመስኖ ግንባታ አፈጻጸምን፣ ያጋጠሙ ችግሮችን፣ ጥንካሬና ድክመቶን አስመልክቶ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን በዚህ በጀት ዓመት በሩብ ዓመቱ የዝግጅት ምዕራፍ በመሆኑ በግንባታ ዘርፍ የተሰራ ሥራ የለም፡፤

### 5.3 የመ/ተ/ግብአት አቅርቦት ሥራዎች አፈጻጸም

**ግብ፡** ቢሮው የሚያከናውናቸውን የጥናትና ዲዛይን እና የግንባታና ግንባታ ክትትል ሥራዎች ለማከናወን ግልጽ ከአድሎ የጸዳ ተጠያቂነትን ያሰፈነ ጨረታ በማውጣትና አሸናፊ በመለየት ውል በመያዝ ግንባታው እንዲሳለጥ ማድረግ፤

**ዝርዝር ተግባራት**

**ሀ. የመስኖና ድሬይኔጅ የግንባታ ክትትል ስራ ግዥ**

- በመንግስት በጀት የ1 መስኖ ፕሮጀክቶች የአማካሪ ግዥ ደባሪ ድሪፕ እና ጠብታ መስኖ ሰርቶ ማሳያ ፕሮጅክት ከልህቀት ዲዛይንና ቁጥጥር ኮረፖሬሽን ጋር ውል ተይዟል
- በመንግስት በጀት የ5 መስኖ ፕሮጀክቶች የአማካሪ ግዥ ከልህቀት ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ኮረፖሬሽን ጋር ውል ተይዟል።
- በመንግስት በጀት የ1 መስኖ ፕሮጀክቶች የአማካሪ ግዥ ከላሊበላ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ሃላፊነቱ የተወሰነ የግ/ማህበር ጋር ውል ለመያዝ የደርድር ስራ እየተሰራ ይገኛል።

**ለ የመስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ስራ ግዥ**

- በአፍሪካ ልማት ባንክ በጀት የ4 የመስኖ ፕሮጀክቶችን የግንባታ ስራ በግልፅ ጨረታ ተቋራጮችን ተጋብዘው፡- ባርጎየ፤ዛሬማ፤አዲቋራይ እና አራዶም በጫራታ ግምገማ ሂደት ይገኛል።

- በአፍሪካ ልማት ባንክ በጀት የ1 መስኖ ፕሮጀክቶችን የግንባታ ስራ ለማሰራት በግልፅ ጨረታ ተቋራጮችን 15753000 ውል ተይዟል፡፡
- በመንግስት በጀት የ4 መስኖ ፕሮጀክቶችን የግንባታ ስራ ለማሰራት በግልፅ ጨረታ ተቋራጮችን ለመጋበዝ ሰነድ ዝግጅት የቴክኒካል ግምገማ ተካሂዶ አንድ ፕሮጀክት ወደ ፍይናንሻል ግምገማ ላይ ይገኛል፡፡
- በመንግስት በጀት የፊጣም ቲሊሊ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የግንባታ ስራ ለማሰራት ከአባይ ኮንስተራክሽን ሃላፊነቱ የተ/ግ/ማህበር ጋር በብር ውል ለመያዝ የደርድር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- በመንግስት በጀት የፊጣም ሰርፀ ወልድ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የግንባታ ስራ ለማሰራት ልህቀት ዲዛይን ኮርፖረሽን ጋር በብር ውል ለመያዝ የደርድር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- በምግብ ማጠናከሪ ፕሮግራም በተገኛ የበጀት ድጋፍ መስኖ ፕሮጀክቶችን የግንባታ ስራ ለማሰራት በግልፅ ጨረታ ተቋራጮችን አሸናፊ ድርጅቶች ተለይተው (ፊጣም ታጂት -2፣ ከንተባ አህቻ እና ጉመራ) ከፋት ጋር በብር 242,805,719.20 ውል ተይዟል፡፡

### ሐ. የመስኖና ድሬይኔጅ ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ስራ ግዥ

- ገምዙ መስኖ ፕሮጅክት የጥናት ከልህቀት ዲዛይንና ቁጥጥር ኮረፖሬሽን ጋር ውል ተወዷል፡፡
- ወለህ ከልህቀት ዲዛይንና ቁጥጥር ኮረፖሬሽን ጋር ውል ለመያዝ የዋጋ ድርድር በማድረግ ይገኛል፡፡
- እንጎችና ጎጣ ከላሊበላ ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ሃላፊነቱ የተወሰነ የግ/ማህበር ጋር ውል ለመያዝ የደርድር ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

**ሰንጠረዥ፡ 1 ውል የተወሰደባቸው ፕሮጀክቶች ዝርዝር**

| የፕሮጀክ ስም | ፕሮጀክት አይነት | ዞን/woreda | የውል መጠን በገንዘብ | ስራው የሚፈጀው ጊዜ | የበጀት ምንጭ |
|---|---|---|---|---|---|
| ደባሪ | የግንባታ ስራ | ማ/ጎንደር/ምስ/በለሳ | 17,753,236 | 10 ወር | ኤዲቢ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፈጣም ታጅት 2 | የግንባታ ስራ | ዋግህምራ/ጻህና | 114910504.7 | 16 ወር | FSRP |
| ከንተባ አህቻ | የግንባታ ስራ | ዋግህምራ/ጻህና | | 14ወር | FSRP |
| ጉመራ | የግንባታ ስራ | ዋግህምራ/ጻህና | **50,573,354.50** | 14 ወር | FSRP |
| ገምዙ | ጥናት ስራ | ማዕ/ጎንደር | 3,510,475.00 | 4ወር | መደበኛ |
| ድምር | | | 264,069,430.2 | | |

### 5.4 የተቋማት አስተዳደርና ጥገና ሥራዎች አፈጻጸም

**ግብ፡** በክልሉ ውስጥ በተገነቡና በሚገነቡ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች 238 የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎችን በማህበር በማደራጀት በአግባቡ እንዲመሩና እንዲተዳደሩ እንዲሁም ጥግና የሚያስፈልጋቸውን 23 ፕሮጀክቶች ጥገና እንዲካሄድላቸው በማድረግ ለተጠቃሚው አርሶ አደር ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤

## ዝርዝር ተግባራት

- በበጀት ዓመቱ 238 እስከዚህ ሩብ ዓመት10 የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን ለማቋቋም ዕቅድ የተያዘ ሲሆን እስከዚህ ሩብ አመት **20** ተቋቀቁሟል፤
- በበጀት ዓመቱ 383 እስከዚህ ሩብ ዓመት 34 ማህበራት ለማጠናከር ዕቅድ የተያዘ ሲሆን እስከዚህ ሩብ ዓመት 74 ማህበር የማጠናከር ስራ ተከናውኗል፤
- በዓመቱ 66 የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማህበራት የኦዲት ስራዎችን ለማከናወን ዕቅድ የተያዘ ሲሆን የዚህ ሩብ አመት እቅድ የለውም ክንውንም አልተፈጸመም፡፡
- በበጀት ዓመቱ 169 ለየወረዳና ለዞን ባለሙያዎች እንዲሁም ለ197 ማህበር አመራር አካላት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት የታቀደ ሲሆን  ለ9 የመሰኖ ማህበራት አመራሮች ስልጠና ተሠጥቷል፤
- 3,252 ኪ.ሜ ዘመናዊና 9785.1 ኪ.ሜ ባህሊዊ የመስኖ አውታር ጠረጋ ስራ ማከናወን በዚህ ሩብ ዓመት 681 ኪ.ሜ ባህላዊ 766 ኪ.ሜ ጠረጋ ለማከናወን እቅድ የተያዘ ሲሆን 284.52 ዘመናዊ ቦይ ጠረጋ የተሳተፈ ማህበረሰብ ወ=5980.73፣ሴ=1188.3 ድምር=7416.03 የተሳተፉ ሲሆን በገንዘብ ሲተመን  2,139,249.00 እንዲሁም  940.75 ባህላዊ ቦይ ጠረጋ የዚህ ሩብ ዓመት ክንውን ሲሆን የተሳተፈ ማህበረሰብ ወ= 10,294.00፣ ሴ= 2,327.00 በድምሩ= 12,621 ተሳትፈዋል በገንዘብ ሲተምን ደግሞ ወደ  2,058,750 ብር የሚገመት ስራ ተከናውኗል፡፡
- የጥገና ስራ የሚከናውንላቸው የመስኖ ተቋማትን የጥናትና ዲዛይን ዶክመንት ማዘጋጀት፤

- ከዞን በተላከው ቅደም ተከተል መሠረት ለእያንዳንዱ ዞን በበጀት ዓመቱ ወደ ጥገና የሚገቡ የጥገና ፕሮጀክቶችን የመለየት ስራ ተከናውኗል፤
- የተለዩ ፕሮጀክቶችን ለእያንዳንዱ ዞን በማሳወቅ የጥናት ሰነዶችን እንዲዘጋጁ ተደርጓል፤
- በ2017 በጀት ዓመት ወደ ጥገና የሚገቡ 15 (939.25 ሄ/ር የማልማት አቅም ያላቸው) በክልል፣ በዞንና ወረዳ ለጠገኑ የታሰቡ የዋጋ ተከላ ስራ እና ንድፍ ስራ በማከናወን ላይ እንገኛለን፡፡
- 8 ነባር በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን ወደ ግንባታ የሚገቡበትን ሁኔታ የማመቻቸት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡
- በ2014 በጀት ዓመት ለዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ከተመደበለት በጀት በተዘዋዋሪ ብድር ለመስኖ ልማት አገልግሎት የሚውል የውሀ መሳቢያ ሞተር ፓምፕ ግዥ በመፈጸም በ2015 እና 2016 ዓ/ም ለአርሶ አደሩ አዝጅ በእጅ በማሰራጨት 78,900,000 ብር በመሰብሰብ በ49,985,874 ለ2017 ለመስኖ ልማት የሚውል 981 የውሀ መሳቢያ ሞተር ፓምፕ ግዥ ተፈጽሞ መስፈርት በማዘጋጀት ለሁሉም ዞኖች ሰቲት ሁመራን ጨምሮ የስርጭት ስራ ተከውኗል፡፡

### 5.5 የዕ/በ/ዝ/ክ/ግ/ ሥራዎች አፈጻጸም

**ግብ፡** የቢሮውን ጥራት ያለው ዕቅድ በማቀድ ታማኒነት ያለው ሪፖርት በማቅረብ፤ በተቋሙ የዕቅድ አፈፃፀም ሂደት የሚታዩ ዉጤታማ ተግባራትን በተሞክሮነት በመቀመርና በማስፋት ሁሉንም የሴክተሩን ተቋማት ወደ ከፍተኛ የአፈፃፀም ደረጃ ማድረስ፤

**ዝርዝር ተግባራት**

- የ2016 ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት እና የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ በማዘጋጀት በዞን፤በወረዳ ማኔጅመንትና በጠቅላላው ሰራተኛ ተገምግሞ የዳበረ ሪፖርት ለመላክ የታቀደ ቢሆንም በወቅቱ የጸጥታ ችግር ምክንያት በቢሮው ሰራተኞች ብቻ ተገምግሞ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፤
- ከፖሊሲ ማትሪክሱ በመነሳት የ2017 በጀት ዓመት እና ከ2018–2022 የ5 ዓመት ስትራተጅክ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡
- የቢሮውን የጸደቀ የካፒታልና ሥራ ማስኬጃ በጀት ቀመር በማዘጋጀት ለቢሮውና ለዞኖች በበጀት ኮድ ተደልድሏል፤በአይቤክስ ተበዝግቧል፤የበጀት ዝውውርም ተከናውኗል፤

- የ2017 በጀት ዓመት የበጀት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ቢሮ በማቅረብ የጸደቀ በጀት ተደልድሏል፤
- በማረጋገጥ ገቢ እንዲሆኑ ተደርጓል፤
- በቢሮዉ የኔትወርክና ሲስተም አስተዳደር ስራን በማጠናከር  የቴክኖሎጅ ነክ ድጋፍ መስጠት ተችሏል፤
- በቢሮው ለተፈቀደላቸው የሥራ ክፍሎች የመደበኛ ስልክ ብልሽት ሲያጋጥም በወቅቱ በማስተካከል አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፤
- ላፕቶፕና ዴስክ ቶፕ ኮምፒዉተሮችን ሙሉ ፕሮገራሙንና ሶፍትዌር በመጫንና በማስተካከል ለስራ ዝግጁ ተደርጓል፤
- በቢሮው የኢንተርኔት አገልግሎት ለሌላቸው በማስገባት ፕሪንተር ሸር የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡
- የኮምፒውተር ማይክሮ ሶፍት ኦፊስ፤ዲፌንደር አንቲቫይረስ ፕሮግራም በማስተካከል ለሥራ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፤
- ብልሽት ያለባቸውን የቢሮ መገልገያ ኤሌክትሮኒክስ የብልሽት ዓይነት በመለየት ለጥገና ዝግጁ ተደርገዋል፤
- የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን በበጀት አስተዳደር ሥራችን በየሩብ ዓመቱ በአይቤክስ ክትትል  ተደርጓል፤
- የቢሮውን ወይብ ሳይት በሳይንስና ቴክኖሎጅ ኮሚሽን ለማስለማት አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብና በመስጠት በማጠናቀቂያ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

### 5.6 የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች አፈጻጸም

**ግብ ፡** በቢሮው ክክልል እስከ ወረዳ ያለውን መዋቅር በመተቀም ያሉ ጸጋወችን በመለየት የቢሮውን ዕቅድ አፈጻጸም  በማስተዋወቅና የተግባቦት ሥራ በመስራት ህ/ሰቡ በመስኖ ልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፤

**ዝርዝር ተግባራት**

- የ2016ዓ.ም አፈጻጸም እንዲሁም የ2017 ዕቀድን አስምልክቶ ለአሚኮ እና ለኢ.ቢ.ሲ. በም/ቢሮ ሃላፊ 1 ጊዜ እንዲሁም በሶስተዮሽ ምክክር መድረክ ዙሪያ 1 ጊዜ የሚዲያ ዘገባዎች በመስጠት አየር ላይ እንዲውል በማድረግ አፈጻጸሙን 100% ማድረስ ተችሏል፡፡
- በአሚኮ እና በኢ.ቢ.ሲ. ሚዲያዎች በ2017 ስለተያዙ የጥናትና ዲዛይን እንዲሁም ግንባታ ዕቅዶችና ስለተያዘላቸው በጀት ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል በሩብ ዓመቱ 1 ጊዜ የታቀደ ሲሆን አፈጻጸሙም 100% ማድረስ ተችሏል፡፡
- በ2016ዓፈጻጸም እና 2017 ዕቅድ ዙሪያ በደሴ ኤፍኤም ሬድዮ ጣቢያ ዘገባ አየር ላይ ውሏል ስለዚህ የሩብ ዓመቱ ዕቅድ 1 ክንውን 1 አፈጻጸም 100%፤
- የተቋሙን ፌስቡክ ገጽ ደንበኞች ቁጥር ከማሳደግ አንጻር በሩብ ዓመቱ 150 በአዲስ ለመጨመር ታቅዶ ክንውን ከነበረው 1400 በሩብ ዓመቱ 200 አዲስ ተከታይ በመጨመር ደንበኞች ቁጥርን ወደ 1600 ማሳደግ ተችሏል ይህም ከዕቅድ አንጻር 133% ተከናውኗል፡፡
- የተለያዩ የተቋሙን ብቻ የሚመለከቱ 60 መረጃዎችን በሩብ ዓመቱ በፌስቡክ ገጽ ለመዘገብ ዕቅድ ተይዞ 30 ዘገባዎች ተሰርተዋል ይህም 50% ተከናውኗል ማለት ነው
- ዌብሳይት የማልማት ስራን በሩብ ዓመቱ መጀመሪያ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር በጋራ በመደጋገፍ ዌብሳይት የማልማት ስራ ተስርቷል በዚህም መሰረት በሩብ ዓመቱ 10 አዳዲስ መረጃዎችን ለመጫን ታቅዶ በሩብ ዓመቱ ብቻ 20 ተጭኗል፡፡ አፈጻጸሙ 200% ነው፡፡
- 12 መምሪያዎች የመምሪያቸው የፌስቡክ ገጽ ያላቸው ሲሆን 10 ታቅዶ ክንውን 4 ነው አፈጻጸም40% ነው፡፡
- 12 መምሪያዎች የመምሪያቸው የፌስቡክ ገጽ ያላቸው ሲሆን 10 ታቅዶ ክንውን 4 ነው አፈጻጸም40% ነው፡፡
- **ብሮሸር 1 ፤በራሪ ወረቀት 1 ተዘጋጅቷል፤**

**ሠንጠረዥ 6. የሶሻል ሚዲያ መረጃዎች**

| ተ.ቁ | የገጹ አይነት | ያለው ደንበኛ ብዛት | በሩብ አመቱ የተጫነ መረጃ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም በ% |
| 1 | ፌስቡክ | 1600 | 100 | 200 | 200 |
| 2 | ቴሌግራም ቻናል | 315 | 10 | 8 | 80 |
| 3 | ቲክቶክ | 1200 | 10 | 5 | 50 |
| 4 | ዩቱብ | 50 | 10 | 0 | 0 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ዋትስ አፕ(ለሃላፊዎች) | 16 | 10 | 10 | 100 |

- የ2017 ዓ.ም ክልል አቀፍ ግምገማ መድረክን አስምልክቶ በሩብ ዓመቱ 1 ታቅዶ ተከናውኗል ስለሆነም አፋጻጸም 100 ፐርሰንት ተከናውኗል፤
- የሶስትዮሽ ምክክር መድረክ መድረኩን በተዋበ መልኩ በማዘጋጀት እንዲሁም ሚዲያና ብሮሽር ጭምር በማዘጋጀት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡
- መረጃዎችን በሶፍት እንዲሁም በሃርድ ኮፒ ጭምር ለማደራጀት ተችሏል የትኛውም ቃላጉባኤ የሚያስፈልጋቸው መድረኮችና ውሳኔዎች በቃለጉባኤ ተሰንደው ተይዘዋል፡
- የመልካም አስተዳደር ዕቅድ ተዘጅቷል፡፡
- የኢትዮጵያን ኮደርስ ኢንሼቲፍ አስምልክቶ ሰራተኛውን በማስተዋወቅ በአጠቃላይ በድምሩ 20 ሰራተኞች ተመዝግበው በመከታተል ላይ ሲሆኑ 7 ሰራተኞች አጠናቀዋል፤
- የተቋሙን አጠቃላይ የመልካም አስተዳዳር ዕቅድ በማዘጋጀት ሂደት ድጋፍ ተደርጓል፤
- ሁሉም ዞን መምሪያዎች የመልካም አስተዳዳር ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ 12 መምሪያ አቅደው እንዲልኩ ማድረግ ተችሏል፤
- አዲስ ዓመትን አስመልከቶ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት በማዘጋጀት በሁሉም ሶሻል ሚዲያ ተሰራጭቷል፤
- ያለፉትን 3 ዓመታት የተቋም ዋና ዋና ስራዎች አፈጻጸም በመጥቀስ ተቋሙን ከአዲስ አመት መልካም ምኞት መልዕክት ጋር አስተዋውቀናል፡፡

## 5.7 የሰው ኃብት ሥራዎች አፈጻጸም

**ግብ፡** የቢሮውን የመፈጸም አቅም ለማሳደግ ቢሮውን ከላይ አስከታች በሰው ሀይል እንዲሟላ በማድረግ በዕውቀት ተመስርቶ ለመስራት እንዲቻል በየደረጃው ለሚገኝ ፈፃሚ ሀይል በየስራ ዘርፉ የሙያ ማነቀቂያ ስልጠናዎች በመስጠት የአቅም ክፍተቱን በመሙላት ወደ ሥራ እንዲገባ በማድረግ ብቃት ያለው ፈጻሚ ማፍራት፡፡

**ዝርዝር ተግባር**

- የቢሮውና በቢሮው የሚገኙ የፕሮጀክቶችን ወ=82 ሴ= 30 ድ=112 የሰው ኃይል መረጃ በጾጥታና ትምህርት ዝግጅት እና በስልጣን እርከን ተደራጅቶ ተይዟል፤

**ሰንጠረዥ፡ 7 የሠው ሀብት መረጃ በጾታ**

| ተ\ቁ | የስራ መደብ | ጠቅላላ የመንግስት ሠራተኞች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ምርመራ |
| 1 | ተሿሚ | 15 | - | 5 | |
| 2 | ዳይሬክተር | 7 | 1 | 8 | |
| 3 | ቡድን መሪ | 1 | 2 | 3 | |
| 4 | ባለሙያ | 58 | 25 | 83 | |
| 5 | የሥ/ም/ማሻሻያ ፕሮጀክት | 4 | 1 | 5 | |
| 7 | ፔሳፒ ፕሮጀክት | 6 | 1 | 7 | |
| | **ድምር** | 91 | 30 | 111 | |

- የቢሮውና በቢሮው የሚገኙ የዞን፤የወረዳና የፕሮጀክቶችን ወ=1,132 ሴ= 407 ድ=1,539 የሰው ኃይል መረጃ በጸታ ተደራጅቶ ተይዟል፤

ሠንጠረዥ 8 ፡ የሰው ኃይል መረጃ በጸታ

| ተ.ቁ | ተቋም | የወረዳ ብዛት | የተፈቀደ | የተሟላ | | | አፈጻጸም በ% | የሴቶች ድርሻ በ% |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወ | ሴ | ድ | | |
| 1 | ቢሮው | | 133 | 71 | 28 | 99 | 74.4 | 21 |
| 2 | ሰ/ወሎ | 11 | 205 | 93 | 40 | 133 | 64.9 | 19.5 |
| 3 | ደ/ወሎ | 20 | 348 | 150 | 43 | 193 | 55.5 | 12.4 |
| 4 | ማዕ/ጎንደር | 15 | 269 | 103 | 46 | 149 | 55.4 | 17.1 |
| 5 | ደ/ጎንደር | 13 | 237 | 111 | 38 | 149 | 62.9 | 16 |
| 6 | ሰ/ሸዋ | 22 | 380 | 153 | 47 | 200 | 52.6 | 12.4 |
| 7 | ምስ/ጎጃም | 17 | 287 | 101 | 51 | 152 | 53 | 17.8 |
| 8 | ምዕ/ጎጃም | 7 | 140 | 58 | 22 | 80 | 57.1 | 15.7 |
| 9 | ምዕ/ጎንደር | 4 | 91` | 22 | 9 | 31 | 34 | 9.9 |
| 10 | ሰ/ጎንደር | 6 | 123 | 44 | 18 | 62 | 50.4 | 14.6 |
| 11 | ሰ/ጎጃም | 7 | 132 | 45 | 19 | 64 | 48.5 | 14.4 |
| 12 | አዊ ብ/ሰብ | 9 | 171 | 70 | 15 | 85 | 49.7 | 8.8 |
| 13 | ዋግኽምራ | 7 | 139 | 59 | 20 | 79 | 56.8 | 14.4 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ኦሮሞ ብ/ሰብ | 5 | 107 | 41 | 9 | 50 | 46.7 | 8.4 |
| 15 | የሥ/ም/ማሻሻያ | | 5 | 4 | 1 | 5 | 100 | 20 |
| 16 | ኢፋድ | | 1 | 1 | 0 | 1 | 100 | 0 |
| 17 | ፔሳፒ | | 7 | 6 | 1 | 7 | 100 | 14.3 |
| **ድምር** | | **153** | **2,684** | **1,132** | **407** | **1,539** | **57.3** | **15.2** |

- በ6 ወሩ የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ማድረግ ካለባቸዉ ሠራተኞች ብዛት ወ= 54 ሴ= 25 ድ= 79 መካከል ብዛት ወ=51 ሴ= 23 ድ= 74 ሠራተኞች ግምገማ ያደረጉ ሲሆን ከፍተኛ ወ= 19 ሴ= 5 ድ= 24 እና መካከለኛ ወ= 32 ሴ= 18 ድ= 50 ውጤት አስመዝግበዋል፡፡
- የሰው ሀብት ስምሪት ስራወችን ማሻሻል በምደባ በቅጥርና ደረጃ ዕድገት ሴ=3 ወ=5 ድ=8 ስምሪት የተፈጸመ ሲሆን 1 ወንድ ባለሙያ በራሱ ፈቃድ ሥራ ለቋል፤
- የወ=17 ሴ=7 ድ=24 የደንብ ልብስ ተጠቃሚ የሆኑ ሰራተኞች መረጃ ተደራጅቶ ተይዟል፤
- የተቋሙን የሰራተኛ ፋይል ከውኃና ኢነርጅ ቢሮ ጋር እርክክብ በማድረግ የሰዉ ሀይል እንዲሁም የግል ፕሮፋይል መረጃ በሀርድና በሶፍት ተጠናክሮ ተይዟል፤

### 5.8 የግዥ፣ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር አፈጻጸም

**ግብ፡** የፋይናንስ፤የንብረት አጠቃቀም፤ የግዥ የውል አስተዳደር አፈፃፀምን ውጤታማነትን፤ የጠቅላላ አግልግሎት ስራን እና የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በማሻሻል የደንበኞችን/የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ፤

**ዝርዝር ተግባር**

- የፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነትን ለማሳደግ ሂሳቦችን በኮዳቸው በሌጀር እና በibex በዚህ ሩብ አመት ውስጥ ተመዝግቦ ክትትል ተደርጓል፤
- ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው መደበኛ የደመወዝ በጀት 2,607,496.73 በዚህ ሩብ አመት ውስጥ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፤
- ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው መደበኛ ስራ ማስኬጃ በጀት 1,034,969.34 በዚህ ሩብ አመት ወር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፤
- ዚህ በጀት አመት ውስጥ ዊዝ ሆልድ፣ሪቴንሽን፣ጡረታ፣ብር 10,373,032.46 ተሰብስቦ ብር 7,036175.72 ለሚመለከተው አካል የገንዘብ ዝውውር ተፈጽሟል፡፡

- በዚህ በጀት አመት ውስጥ ከተቋራጮች፡ኢንተር ፕራይዝ፣ ከአማካሪ ድርጅት በቅድሚያ ክፍያ ከተሰጠ ብር 1,873,084,003.96 ላይ ብር 324,124,386.44 ገንዘብ ተመላሽ ተደርጓል፡
- በአምባሰል ድርጅት የተገዙ የናፍጣ ውሃ መሳቢያ ሞተር ፓንፕ እና ዴሊቨሪ ሆዝ 981 49,985,874 ግዥ በመግዛት ክፍያ መፈጸሙ፡
- የባንክ ሂሳብ ማስታረቅ በዚህ ሩብ አመት ውስጥ ከባንክ ስቴትመንት በማምጣት በባንክ የወጡ ሂሳቦችን በማናበብ 3 ጊዜ ሪፖርት ተሰርቷል፤
- ተከፋይ እና ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በእድሜ በመለየት ለሚመለከተው አካል እንዲላክ ተደርጓል፡፡
- በአመተዊ እቅድ የተገዙ ንብረቶችን በባለሙያ በማረጋገጥ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ እንዲሆን ተደርጓል፤ንብረቶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ፍታዊ የንብረት ክፍፍል ተደርጋል፤
- የንብረት መመዝገቢያ ፎርማቶችን በማደራጀት ንብረቶችን ቢንና ስቶክ ካርድ በማዘጋጀት በየወሩ ባላንስ / የምዝገባ / ስራ ተሰርቷል፤የመንግስት ንብረቶችን ለመንግስት ስራ ብቻ እንዲውሉ የቁጥጥር ስራ በመስራት ከአንድ በላይ በስማቸው የተያዘ ላብቶፕ ተመላሽ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፤አመታዊ ንብረት ቆጠራ ኮሚቴ በማዋቀር ቋሚ እና አላቂ ንብረት በመቆጠር ባለንስ መስራት እና ንብረተቸ ኮድ የመስጠት ስራ ተሰርቷል፡፡
- ከአንባሰል ድርጅት የተገዙ የናፍጣ የውሃ መሳቢያ ሞተር ፓንፕ 981 በብር 49,985,874 በአረጋጋጭ ኮሚቴ ተረጋግጦ ንብረት ክፍል ገቢ ተደርጓል፡፡አዳዲስ የተገዙ ንብረቶችን በእቃ ዝርዝር መሰረት ገቢና ወጭ ተሰርቷል፡፡
- የበጀት ዓመቱን የግዥ ፍላጎት በማሰባሰብ የማደራጀት ስራ እና በማኔጅመት አጸድቆ ጨረታ እንዲወጣ የዝግጅት ስራ ታሰርቷል፤ግልጽ ጨረታ በማውጣት የቢሮ ጽዳት፤ግዥ ተፈጽሟል፤የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ ተፈጽሟል፡፡
- የነዳጅ፣አመታዊ ግዥ መስተንግዶ፤ህትመት ግዥ ተፈጽሟል፤የቢሮ ክራይ፡ አመታዊ የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ፣መኪና ጥገና፣ለጉልበት ሰራተኛ፣የሞባል ካርድ ግዥ ተፈጽሟል፡፡
- በሩብ አመቱ ውስጥ የቢሮ ጽዳት፣ነዳጅ፣ቢሮ ክራይ፣መድን፣ የቢሮ ህትመት ውል በመያዝ ስራወች እንዲሰሩ ተደርገዋል ፡፡የመኪኖች ሰርቪስ ጥገና አመታዊ ውል አሸናፊ

ከሆነው ድርጅት ጋር መኪኖች እንደብልሽታቸው መጠን በሩብ አመቱ ውስጥ በውላቸው መሰረት እንደ ብልሽታቸው መጠን ጥገና ተደርጓል፡፡

- የተሽከርካሪ ነዳጅና ቅባት በኖርማላይዜሽኑ መሰረት ለመሙላት ታቅዶ በታቀደው መሰረት ለከተማ በሚቀርበው ስምሪት መሰረት ነዳጅ ተሞልቷል፤የቢሮ ጽዳት አቅርቦቱንና የቢሮው ክፍሎች በጥራት መጸዳታቸውን በመከታተል በተፈረመው ውል መሰረት መሰራቱን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፤ከክፍል ወደ ክፍል የሚደርሱ ደብዳቤዎችን ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲደርሱ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል፤
- ገቢና ወጭ የተፈፀመባቸው ሰነዶች መረጃ በቅደም ተከተል ሰንዶችን በሀርድና በሶፍት ኮፒ ተደራጅቶ ተይዟል፤
- በDebit Advice የገቢና ወጭ ሰነዶች መረጃ በሀርድና በሶፍት ኮፒ ተመዝግበው ተይዘዋል፤
- በቢሮ ውስጥ ያሉ ንብረቶችን ለቆጠራ እና ለሶስተኛ ወገን በሀርድ አና ሶፍት ኮፒ በቢን ካርድ፣እስቶክ ካርድ እና ዩዘር ካርድ አደራጅቶና በመዝገብ እንዲያዝ የቅድመ ዝግጅት ስራ ተሰርቷል፡፡

## 5.9 ባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች አፈጻጸም

**ግብ፡** *የሥራ ዕድል ፈጠራ፤የሥርዓተ-ጾታና ማህበራዊ ጉዳዮች፤ኤችአይቪ/ኤዶስ እና አካባቢ ጥበቃ ተግባራትን በማካተትና በመፈጸም ለክልላችን ብሎም ለሀገራችን ለውጥ ማምጣት፤*

**ዝርዝር ተግባራት**

***ሀ. ኤች አይ ቪ/ኤድስ***

- ቢሮው ካለው በጀት 2% መድቦ ኤችአይቪ/ኤድስን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሜንስተሪሚንግ ሥራውን በዕቅዱ አካቶ እየተፈጸመ ለወ=78 ሴ=27 ድ=111 የቢሮው ሰራተኞች በኤችአይቪ/ኤድስ ዙሪያ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ የሚሰራ ይሆናል፤
- ቢሮው የኤድስ ፈንድ በማቋቋም ከ99 ሰራተኞች በየወሩ በፈቃደኝነት ከደመወዝ እየተቆረጠ ወላጅ አልባ ህፃናትን ለመርዳት 3 አባላት ያሉት ኮሚቴ በማዋቀር እንቅስቃሴ እየተደረገ ሲሆን ብር 1,500.00 እየተሰበሰበ ለተረከብናቸው 2 ህጻናት ድጋፍ እየተደረገ ነው፡፡

***ለ. ሥርዓተ ጾታ***

- ቢሮው በጀት መድቦና የሥርዓተ ጾታንና የማህበራዊ ጉዳዮች ሜንስተሪሚንግ ሥራውን በዕቅዱ አካቶ በጀት በመመደብ እየሰራ ይገኛል፤
- ይህን ተግባር ክትትል የሚያደርግ ባለሙያ ባይኖርም ፎካል ፐርሰን በሴቶች አስመርጧል፤
- ሴቶችን በመመሪያ 20/80 መሰረት በልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ ለማድረግም ጥረት ይደረጋል፤

### ሐ. የሥራ ዕድል ፈጠራ

በቢሮው ሥር በሚካሄዱ የመስኖ ፕሮጀክቶች ለወ= 26,000 ሴ= 20,000 ድ=46,000 ቋሚና ጊዜዊ ለወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ እየተሰራ ሲሆን ቢሮው የሚሰራቸው ግንባታዎች የዝግጅት ምዕራፍ በመሆኑ የተፈጠረ የሥራ ዕድል የለም፤

## 6 የነበሩ ጥንካሬና ድክመቶች

### ሀ. ጥንካሬ

- የአመለካከት፣የክህሎት ክፍተቶችን ለመሙላት የሚደረገው ጥረት መኖሩ፤የሥራ ማጓተትን መቅረፍ የሚያስችል ጥረት መኖሩ፤የሥራ ተነሳሽነት በሁሉም ባለሙያዎች ጋር መኖሩ፤ሥራን አቅዶና ቆጥሮ ይዞ በተናጠልና በቡድን ተጋግዞ የመሥራትና የህዝብ አገልጋይነት ስሜት እያደገ መምጣት፤
- በለው የሰው ኃይል ስራውን መስራት መቻል፣የቢሮ ቁሳቁሶች ባለመሞላታቸው ምክንያት በትውስት ስራውን መስራት መቻል፤
- የተጠየቁ ክፍያዎችን በወቅቱ መስራት፣
- በዳይሬክተር ደረጃ በየ15 ቀናት ውይይት በማድረግ ስራዎችን በተሻለ መልኩ ለምስራት ጥረት ተደርጓል፣
- መሰረታዊ የመስኖ ፕሮጅክቶች መረጃ ጥራት መሻሻል፣
- በተቋራጭና አማካሪ ለሚጠየቁ የተለያዩ ጥያቄዎች ፈጣን ምላሽ በመስጠት በኩል መሻሻል መኖር፤
- የውኃ መሳቢያ ሞተር ፓምፖችን ግዥ መፈጸም መቻሉ፤
- የጥገና ፕሮጀክቶችን ወቅቱን ጠብቀን የመለየት ስራ መስራታችን እና ለዞኖች ማሳወቃችን

### ለ. ድክመት

- የሥራ ውይይት ሳይቆራረጥ ለማድረግ ውስንነት መኖሩ፤ተገልጋዮች የጽሁፍ አስተያየት እንዲሰጡ ውስንነት መኖሩ ፤
- በወቅታዊ ችግር ምክንያት መረጃዎችን አጠናክሮ ለመያዝና በመስክ በመገኘት ድጋፍና ክትትል ለማድረግ አለመቻል፤የተጠናከረ መረጃ አለመያዝ፤
- የአነስተኛ መስኖ ፕሮጅክቶች የክፍያ ጥያቄዎች ወጥ የሆነ አሰራር ማስቀመጥ አለመቻል፤
- መረጃዎችን በተደራጀ መልኩ አለመያዝ፤
- የስራ እቅዶችን በተያዘላቸው ጊዜ ያለመከታተልና ያለመፈጸም፣
- በተለዩ ምክንያቶች የኮንትራት አስተዳደርን መተግበር አለመቻል በተለይ የልማት ድርጅቶች የሚሰሯቸውን የግንባታ ፕሮጀክቶች፤
- የሞተር ፓምፕ ስልጠና አለመሰጠቱ ሞተር ፓምፖችን በሙሉ አቅም ወደ ስራ ለማስገባት መቸገራችን፤
- ዞኖች ጥራቱን የጠበቀ ሪፖርት አለመላክ አዲስ ለዞኖች የተመደቡ የውሃ መሳቢያ ሞተር ፓምፖች ወደ ተመደደቡት ዞኖች አለመሰራጨታቸው፤
- በ2016 ገንዘብ ቢሮ ለስልጠና የተጠየቀ ገንዘብ አለመፈቀዱ እና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ የማህበር አመራሮች የአቅም ውስንነት መኖሩ፤
- የጸጥታ ችግር መኖር በዚህም ምክንያት ተከታታይነት ያለው ድጋፍ አለማድረግ፤

## 7 ያጋጠሙ ዋናዋና ችግሮችና የተወሰደ መፍትሄና የበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

### ሀ. ያጋጠሙ ችግሮች

- ❖ ክልሉን ባጋጠመው የሰላም መደፍረስና የፀጥታ ችግር ምክንያት በተፈለገው ጊዜና ወቅት ተንቀሳቅሶ የድጋፍና ክትትል ስራ መስራት አለመቻሉ::
- ❖ አንዳንድ ዞኖች በተፈጠረው የፀጥታ ችግር ምክንያት የቢሮ ቁሳቁሶች በመዘረፋቸው የጥናትና ዲዛይን ስራ ለመስራት ተቸግረዋል (ኮምፒተር)::
- ❖ በዕቅዳችን ላይ ባስቀመጥነው የተግባር ምዕራፍ መሰረት ተቋማዊ ስራዎቻችንን ማከናዎን አለመቻላችን::
- ❖ አንዳንድ ፕሮጀክቶች በካሳና በአላግባብ ጥቅም ፍላጊዎች ምክንያት በተቀመጠላቸው ጊዜ መጠናቀቅ አለመቻል::

- ❖ የግንባታ ስራዎችን ለመጀመር በክልሉ ያለው የጸጥታ ችግር እየተባባሰ መምጣት፣
- ❖ የተሰሩ ስራዎችን ክፍያ ለመፈጸም የዘላቂ ልማት ግብ በጀት መዘግየትና ከተቋራጮች ክፍተኛ ቅሬታ መቅረብ፣ በተለይ በወረዳ ደረጃ በወጣቶች የተሰሩ ስራዎች፣
- ❖ የዲዛይን ክፍተት መኖርና በግንባታ ወቅት የዲዛይን ማሻሻያ በመብዛቱ የስራ መዘግየትና ተጨሪ ወጭ መኖር (ሚሌ ኮትቻ፣ ጀልደቲ፣ ግልገል አባይ፣ ፈጣም፣ ማመጫ ገዳም፣ አልዋዲ፣ ሰርጸወልድ፣አይራራ፣አጼውሃ፣ ከሰም ምንጭ)
  - ❖ በተደጋጋሚ ቅሬታ የሚነሳባቸውና የግንባታ ችግር ያለባቸው ፕሮጀክቶች ፕግንባታ ስራ ማስቀጠልና መፍትሄ መስጠት ያለመቻል
  - ❖ በወረዳ ደረጃ በግንባታ ላይ የነበሩና ውላቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች ወደ መልሶ ግንባታ ለማስገባተ የተሟላ ስነድ አለመቅረብ /ማዕከላዊ ጎንደር 4፣ ደቡብ ወሎ 1 ፣ ኦሮሚያ 2 ፣ ሰሜን ጎንደር 1/

**ለ. የተወሰደ የመፍትሄ እርምጃ**

- ❖ በስልክ የመረጃ ልውውጥ በመድረግ ስራ ለመስራት ተሞክሯል፡፡
- ❖ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ተግባራትን ለማከናውን ጥረት ተደርጓል፤
- ❖ ክልሉን ባጋጠመው የፀጥታ ችግር በመንግስት መኪና ተንቀሳቅሶ ለዞኖችና ወረዳዎች ድጋፍ ማድረግ አስቸጋሪ ቢሆንም በግል ትራንስፖርት ተንቀሳቅሶ የተለያዩ ድጋፎችን ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

**መ. የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች**

- ➢ የወረዳ፤የዞንና የክልልን ፈፃሚ ሃይል በአመለካከትና በክህሎት ገንብቶ ወደ ሥራ ማስገባት፡፡
- ➢ ክልሉን በገጠመው የፀጥታ ችግር ምክንያት ያለ ሥራ ያለፉ ጊዚያቶችን ጨምሮ ሰላሙ እንደተመለሰ በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ ወደ ሥራ መግባትና የአመቱን ዕቅድ በውጤት ማጠናቀቅ፡፡
- ➢ በአማካሪ ድርጅቶች፤በወረዳዎችና ዞኖች ደረጃ በሚሰሩ የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች ላይ ችግር ፈችና ውጤታማ የሆነ የድጋፍና ክትትል ሥራ መስራት፡፡
- ➢ የ2017 ዓ/ም ግዥዎችን ፈጥኖ በመፈፀም ለበጀት ዓመቱ አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ፤በ2017 ለቢሮ የሚመደብ SDG፤መደበኛ አካውንት እና ሌሎች ፕሮጀክቶች ለግንባታ፤ለጥናት እና ዲዛይን ለዚህ ስራ ማስፈጸሚያ የሚመደብ በጀት ቀልጣፋ ጥራት ባለው በሆነ መልኩ ክፍያ መፈጸም፡፡

- ለባለሙያዎች ሙያዊ የሆነ ስልጠና በወቅቱ መስጠት ፤
- የቢሮ ቁሳቁሶች ማሟላት ፤
- የጸደቁ የግንባታ ክፍያዎች በተቻል አቅም በጀት እንዲለቀቅ ማድረግና ክፍያዎችን በመፈጸም ስራ በሚያሰሩ አካባቢዎች ስራዎችን እንዲጀመሩ ማድርግ (በተለይ በተደራጁ ወጣቶች የሚሰሩ ስራዎች)
- በተቋራጭና በአማካሪ ድርጅቶች በኩል የሚሰሩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን የማጠናቀቅ ስራ ፈጥኖ መሰራት፣
- ሊያሰሩ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን በመለየት በዞንና ወረዳ በኩል ክትትል በማድረግ ሰራዎችን ማስጀመር፣
- የረድኤት ድርጅቶችን እቅድ በመገምገም በልዩ ትኩረት በመደገፍ ፈጥነው ወደስራ እንዲገቡና የተመደበውን በጀትና ጊዜ በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል
- በ2015 በጀት ዓመት የግንባታ ውል የተያዘላቸውና ወደ ግንባታ ያለገቡ (አልዋዲ፣ሰርጸ ወልድ፣ ጅማ ፈዘዝ) እንዲሁም ግንባታቸው ተጀምሮ በተለያየ ምክንያት የቆሙ (በልጨት) መስኖ ፕሮጀክቶች ላይ ከወዲሁ የመፍትሄ/የውሳኔ ሃሳብ ማሰቀመጥ፣
- ከወረዳ ጅምሮ በተመረጡ የስልጠና አይነቶች ለባለሙያዎች የአቅም ግንባታ መሰጠት
- ለቢሮው የሰው ኃይል  በልዩ ሁኔታ በማስፈቀድ ማሟላት፤
- የግንባታ ዕቃዎች ወቅታዊ ዋጋ በየሩብ ዓመቱ  በማጠናት መረጃ መያዝ፤